**ህዝበ-ወሳኔን ማክበር ማስልጠን ነው!**

**ዘአማን በላይ 09-27-17**

መስከረም 7 ቀን 2010 ዓ.ም. የቅማንትና የአማራ ህዝቦች ተቀላቅለው ከሚኖሩባቸው 12 ቀበሌዎች ወስጥ በስምንቱ ቀበሌዎች በተከናወነው የድምፅ አሰጣጥ ከ90 በመቶ በላይ ሚራጩ ህዝብ ድምፅ ማስጠቱ ይታወቃል። ይሁንና ጉዳዩን ባስፈፀመው የኢትዮጵያ ምርጫቦርድ በኩል ምንምዓይነት መግለጫ ሳይሰጥ የህዝቦችን አንድነት የሚፈልገው ፅንፈኛው ሃይል ከወዲሁ የራሱን ግምት በማስቀመጥ ለብጥብጥ ጉዳዩን ሊጠቀምበት እየሞከረ ነው።

ዳሩ ግን ፅንፈኛው አካል ያሻወን የቅጥፈት ፕሮፖጋንዳ ቢያራምድም የሀገራችን ህዝብ የየትኛውንም ቀበሌ ህዝበ- ወሳኔን ማክበር የስልጡኔ ምልክት መሆኑን የሚገነዘብ ነው። እንዲሁም የየትኛውም አካባቢ ህዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን ህገ መንግስታዊ መብቱን ተጠቅሞ የሰጠወን ወሳኔ ማክበር ለጠንካራ የህዝቦች አንድነትና አብሮነት ማሳረታዊ ጉዳይ መሆኑን በሚገባ ያወቃል።

በፌደራ ህገ መንግስት አንቀፅ ስምንት ላይ እንደተማለከተው፤ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት መሆናቸወንና ሉዓላዊነታቸው የሚገለፀወም በህገ-መንግስቱ ማሳረት በሚምርጧቸው ተወካዮቻቸወና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት እንደሚሆን ደንግጓል።

ይህ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ በግልፅ እንደሚያሳየው ማንኛውም የፖለቲካ ስልጣን የሚያዘው የሉዓላዊ ስልጣኑ ባለቤት በሆነው ህዝብ ይሁንታ ብቻ መሆኑን ነው። ህዝቡ ሲፈልግ ይሾማል፤ ሳይፈልግ ደግሞ ይሽራል። ይህን መብት ለህዝቦች የሰጡት ራሳቸው ህዝቦች ናቸው። ሌላ የትኛውም ወገን አይደለም። እናም አማራና ቅማንት ተቀላቅለው በሚኖሩባቸው ስምንት ቀበሌዎች ወስጥ የተካሄደው ህዝበ-ወሳኔ ከዚህ አኳያ የሚምዝን ነው።

ርግጥ በህገ መንግስቱ የተለያዩ አንቀፆች ወስጥ የተቀመጡት ሁሉም መብቶች የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በትግላቸው የተጎናፀፏቸው ትሩፋቶች ናቸው። እነዚህን ህገ መንግስቱ ያረጋገጠላቸወን መብቶች ተጠቅመወም የበርካታ ትሩፋቶች ባለቤቶች መሆን ችለዋል። የአማራና የቅማንት ህዝቦችም እነዚህን ትሩፋቶች እያጣጣሙ ናቸው። በህገ መንግስቱ ላይ ለራሳቸው የሰጡትን መብት እየተጠቀሙበት ነው። ሌላ ምንምዓይነት ተልዕኮ ያለው አይደለም።

ታዲያ እዚህ ላይ መብትንና ብሔራዊ መግባባትን ማጣረስ አይገባም። የአማራና የቅማንት ህዝቦች ጉዳይ ህገ መንግስታዊ ነው። አሁንም 'ብሔራዊ መግባባት አልተፈጠረም' የሚያስብል አይደለም። ርግጥ እዚህ ሀገር ወስጥ ህዝቡ የሚግባባቸው በርካታ የብሔራዊ መግባባት ጉዳዮች አሉ። የህዳሴው ግድብ ከእነዚህ ጉዳዮች ወስጥ የሚጠቀስ ነው።

ለነገሩ በዓለም ላይ ያለ ማንኛውም ህዝብ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ሊግባባ አይችልም። እንኳንስ ህዝብን የሚያክል ትልቅ የማህበረሰብ ስብስብ ቀርቶ፤ በቤተሰብ ወስጥም ቢሆን ባልና ሚስት፣ ወንድምና እህትም ቢሆኑ በሁሉም ጉዳዮች ሊግባቡ አይችሉም።

በማህበረሰብም ይሁን በቤተሰብ ወስጥ ልዩነት ያለና የነበረ፣ ወደፊትም የሚኖር ነው። እናም ብሔራዊ መግባባት ማለት አብዛኛው ህዝብ በአብዛኛው ጉዳይ የጋራ አተያይን እንዲያዳብር ማድረግ መሆኑን ማዝንጋት አይገባም። በዚህም ከሀገር ሉዓላዊነትና ዕድገት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ማከናወን የተቻለ ይመስለኛል።

እናም አንድ ህዝብ ህዝበ ወሳኔ አካሂዳለው በማለት ህገ መንገስታዊ መብቱን ሲጠቀም ከሜሬት ተነስቶ ጉዳዩን ከበሔራዊ መግባባት ጋር ለማጣመር ማጣከር ስህተት ይመስለኛል። ህዝበ ወሳኔን ማካሄድም ይሁን ወጤቱን በፀጋ መቀበል የማስልጠን ምልክት ነው።

ሀገራችን ወስጥ የየትኛወም ህዝብ ህጋዊ መብት ተከብሯል። ለአማራና ለቅማንት ህዝቦች ተለይቶ የሚከለከል አይደለም። ህገ መንግስታዊ መብታቸው ነው። ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ የህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩበት፣ ለደሞክራሲያው አንድነት ማስረት የተጣለበት፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማንነት፣ ወብትና ህብረት የታየበት ብሎም የቀደምት ስልጣኔ ባለቤት መሆናቸወም የተረጋገጠበት፣ የልማታዊና ደሞክራሲያዊ ሥርዓተ ግንባታ ጉዞ የተጀመረበት ማስረቱ ይኸው ህገ መንግስትና ለህገ መንግስቱ ዘብ የቆመ ጠንካራ አማራርና ህዝብ ነው። በእኔ እምነት የአማራና የቅማንት ህዝቦች ጉዳይ የዚህ እወነታ ነፀብራቅ ነው።

የህገ መንግስቱ ድሎችና ወጤቶች ከመቼወም በላይ ተስፋፍተው፣ የዜጎች ማንነትና ባህላዊ እሴቶች ጎልተው ወጥተው፣ ሜልካም ተሞክሮዎችም ይበልጡኑ ጎልብተው፣ የአንድነታችንና የጥንካሬያችን መለጫ ሆነው እንዲቀጥሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው ጉዟቸውን ቀጥለዋል። በእኔ እምነት የአማራና የቅማንት ህዝቦች ጉዳይ የዚህ እወነታ ነፀብራቅ ነው። እናም መብቶቻቸው በፅንፈኞች ዋይ…ዋይታ የሚጣል አይደለም።

ዛሬ ኢትዮጵያ ወስጥ የእኩልነት መብት ሚረጋገጫ የሆኑት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ ታሪኮች…ወዘተ ተከብረዋል፡ ፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በፖለቲካዊ አስተዳደር በኩል እኩል የመሳተፍ መብት ያገኙ ሲሆን፤ በልማት ስራው ላይም እኩል ዕድል እዲያገኙና በወጤታቸው ማስረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተችሏል፡ ፡

በመሆኑም አንዳንድ ወገኖች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ላይ ያላቸው የስጋት ምንጭ ቀዳሚዎቹን አሃዳዊ ስርዓቶች ከመናፈቅ የመጣ አሊያም ህገ መንግስቱን ቀድዶ ለመጣል ከሚፈለግ የመነጨ ከመሆኑ በስተቀር እስካሁን ድረስ ያለው ተጨባጭ እወነታ የሚባታተን ስጋትን የሚያመላክት አይደለም።

ምንም እንኳን የመገንጠል ጥያቄ ሊኖር የሚችለው በፌደራል ስርዓቱ ወስጥ ነው ተብሎ ቢታሰብም እስካሁን ድረስ ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሚያመላክተው አብዛኛዎቹ አሃዳዊ መንግስታት ማባታተናቸውን ነው። እግርጥም “አራምባና ቆቦ” ስጋት ይሏል እንዲህ ነው።

ያም ሆነ ይህ፤ በፌደራሊዝም ስርዓታችን ማዕቀፍ ወስጥ የሚገኘው የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የአንድነታችን ዋስትና እንጂ የማለያየታችን ስጋት ሊሆን አይችልም። በአፍሪካ ወስጥ የሚገኙና ይህ አንቀጽ የሌላቸው ሀገራት

በብጥብጥና በሁከት እየታመሱ ያሉትም በሚፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነትን ማምጣት ባለመቻላቸው መሆኑን ካሉበት ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ መመልከት ተገቢነው።

የአማራንና የቅማንትን ህዝብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትም የህዝቦችን በሚፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነትን የሚያረጋግጥ እንጂ ለማብታተን ምክንያት የሚሆን አይደለም። የህዝቦችን መብት ማክበርና ፍላጎታቸውን ሚረጋገጥ የስልጣኔ ምልክት እንጂ በሌላ መንገድ የሚዟረንም አይደለም። እናም የህዝበ ውሳኔ ውውጤት ተዋረዱን ጠብቆ በሚገለፅበት ወቅት ውጤቱን በፀጋ መቀበል ያስፈልጋል።